ይህ ሰነድ በHUD የወጣው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም ያዘጋጀልዎ መብትና ግዴታዎን በቀላሉ እንዲያውቁ እርስዎን ለመርዳት በማሰብ ብቻ ነው። የዚህ ሰነድ ኦፊሴላዊ፣ ሕጋዊና ገዥ ቅጂ በእንግሊዝኛ የተዘጋጀው ይሆናል። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።

OMB Control # 2502-0581
Exp. (07/31/2012)

# በHUD ለሚታገዙ ቤቶች አመልካቾች የሚሰጥ የተጨማሪና አማራጭ የአድራሻ መረጃ

## በፌደራል ደረጃ ለሚታገዙ መኖሪያዎች የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ተጨማሪ ክፍል

ይህ ቅጽ ለእያንዳንዱ በፌደራል ደረጃ ለሚታገዙ መኖሪያዎች አመልካች የሚሰጥ ነው

***መመሪያዎች፡ አማራጭ የግለሰብ ወይም የድርጅት አድራሻዎች፡*** ለመኖሪያ ቤት ከሚያቀርቡት ማመልከቻ ጋር የቤተሰብ አባልዎን፣ የጓደኛዎን ወይም የማኅበራዊ ወይም የጤና ድጋፍ ሰጪዎን ወይም ሌላ የድርጅት ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የማካተት መብትዎ በሕግ የተጠበቀ ነው። ይህ የአድራሻ መረጃ ዓላማው በኪራይ ዘመንዎ ወቅት ለሚነሱ ጉዳዮች እልባት በመስጠት ወይም የሚያስፈልግዎትን ማንኛውንም ልዩ እንክብካቤ በማግኘት ረገድ ሊያግዝዎ የሚችል ግለሰብ ወይም ድርጅት ማግኘት የሚችሉበትን የአድራሻ መረጃ መስጠት ነው። **በዚህ ቅጽ ላይ የሚሰጡትን መረጃ በማንኛውም ጊዜ ማሻሻል፣ ማስወገድ ወይም መቀየር ይችላሉ።** ይህንን የአድራሻ መረጃ መስጠትዎ ግዴታ አይደለም፤ ሆኖም መረጃውን ለመስጠት ከመረጡ እባክዎን አግባብ ያለውን መረጃ በሙሉ ያካትቱ።

| | |
|---|---|
| **የአመልካች ስም፡** | |
| **የፖስታ አድራሻ፡** | |
| **የስልክ ቁጥር፡** | **የሞባይል ስልክ ቁጥር፡** |
| **የተጨማሪ ግለሰብ ወይም ድርጅት አድራሻ፡** | |
| **አድራሻ፡** | |
| **የስልክ ቁጥር** | **የሞባይል ስልክ ቁጥር፡** |
| **የኢ-ሜል አድራሻ (ካለ)፡** | |
| **ከአመልካች ጋር ያለው ዝምድና፡** | |

**አድራሻው የሚያገለግልበት ምክንያት፡** (ተገቢ የሆነው ላይ ሁሉ ምልክት ያድርጉ)

- ☐ በአደጋ ጊዜ
- ☐ እርስዎን ማግኘት ሳይቻል ሲቀር
- ☐ የኪራይ እገዛው ሲቋረጥ
- ☐ ከዩኒቱ ሲባረሩ
- ☐ የኪራይ ክፍያ ሲዘገይ
- ☐ በዳግም ማረጋገጫው ሂደት ለማገዝ
- ☐ የኪራይ ጊዜው ሲለወጥ
- ☐ የቤቱ ደንብ ሲለወጥ
- ☐ ሌላ፡ ________________________________________

**የቤቶች ጉዳይ ባለሥልጣን ወይም ባለቤት ግዴታዎች፡** መኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ፈቃድ ካገኙ፣ ይህ መረጃ የኪራይ ፋይልዎ አካል ሆኖ ይቀመጣል። በኪራይ ዘመንዎ ወቅት የሚነሱ ጉዳዮች ካሉ ወይም የሚፈልጉት አገልግሎት ወይም ማንኛውም ልዩ እንክብካቤ ካለ የጠቀሱትን ግለሰብ ወይም ድርጅት በማነጋገር ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ወይም የሚያስፈልግዎትን ልዩ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማድረግ እንጥራለን።

**ምሥጢር አጠባበቅን የሚመለከት መግለጫ፡** በዚህ ቅጽ ላይ የሰፈረው መረጃ ምሥጢራዊ ሲሆን በአመልካቹ ወይም አግባብ ባለው ሕግ ካልተፈቀደ በቀር ይፋ አይደረግም።

**ሕጋዊ ማሳሰቢያዎች፡** የቤቶችና ማኅበረሰብ ልማት ደንብ 1992 ክፍል 644 (Section 644 of the Housing and Community Development Act of 1992) (የሕዝባዊ አስተዳደር ሕግ 102-550፣ እ.ኤ.አ. በጥቅምት 28፣ 1992 የጸደቀ) (Public Law 102-550, approved October 28, 1992) በፌደራል ደረጃ ለሚታገዙ መኖሪያ ቤቶች የሚያመለክተው እያንዳንዱ ሰው፣ ስለ ተጨማሪ ግለሰብ ወይም ድርጅት መረጃ መስጠት የሚችልበት አማራጭ እንዲቀርብለት ይጠይቃል። የመኖሪያ ቤት አገልግሎት ሰጪው የአመልካቹን ማመልከቻ ሲቀበል በሚዛናዊ የቤቶች አስተዳደር ደንብ (Fair Housing Act) እንዲሁም በእድሜ ረገድ የሚፈጸም መድልዎን በሚከለክለው የእድሜ መድልዎ ደንብ 1975 (Age Discrimination Act of 1975) መሠረት በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በብሔራዊ ማንነት፣ በጾታ፣ በአካል ጉዳተኝነት እና በቤተሰብ ሁኔታ ምክንያት በፌደራል ደረጃ እገዛ ወደሚሰጥባቸው መኖሪያዎች እንዳይገቡ ወይም እንዳይሳተፉ አድልዎ ማድረግን የሚከለክለውን ጨምሮ ከአድልዎ ነፃ የሆነ እኩል አጋጣሚ መስጠትን የሚደነግገውን 24 CFR section 5.105 ለማክበር መስማማቱ ነው።

☐ የአድራሻ መረጃውን መስጠት ካልፈለጉ እዚህ ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ።

| | |
|---|---|
| | |

የፊርማው ቦታ ጠፍቷል

በዚህ ቅጽ ላይ መረጃ ማሰባሰብን በተመለከተ የሰፈረው መስፈርት የወረቀት ሥራን ለመቀነስ በወጣው ደንብ 1995 (Paperwork Reduction Act of 1995 (44 U.S.C. 3501-3520)) መሠረት ለአስተዳደርና በጀት ቢሮ (Office of Management and Budget (OMB)) ተልኳል። የሕዝብ ሪፖርት የሥራ ጫና መመሪያዎችን ለመከለስ፣ ነባር የመረጃ ምንጮችን ለመፈለግ፣ አስፈላጊውን መረጃ ለማሰባሰብና ለማስተካከል እንዲሁም የመረጃ ስብስቡን ለማጠናቀቅና መልሶ ለመገምገም የሚወስደውን ጊዜ ጨምሮ ለአንድ ምላሽ የሚያስፈልገው ጊዜ አሥራ አምስት ደቂቃ እንደሚሆን ተገምቷል። የመኖሪያ ቤቶችና የማኅበረሰብ ልማት ደንብ 1992 ክፍል 644 (Section 644 of the Housing and Community Development Act of 1992 (42 U.S.C. 13604)) በHUD በሚታገዙ የመኖሪያ ቤቶች ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ የመኖሪያ ቤት አገልግሎት ሰጪዎች በHUD የሚታገዙ ቤቶችን በተመለከተ ማመልከቻ ለሚያስገባ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ቤተሰብ በማመልከቻው ላይ የቤተሰብ አባላቸውን፣ የጓደኛቸውን ወይም ከማኅበራዊ ወይም ጤና እገዛ ጋር ወይም ከተመሳሳይ ድርጅት ጋር ግንኙነት ያለውን ግለሰብ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች መስጠት የሚችሉበት አማራጭ እንዲቀር የማድረግ ኃላፊነት ተጥሎበታል። እንዲህ ያለው መረጃ የሚሰጥበት ዓላማ የመኖሪያ ቤት አገልግሎት ሰጪው ተከራዩ ማንኛውንም አገልግሎት ወይም ልዩ እንክብካቤ ለተከራዩ በመስጠት እንዲሁም በኪራይ ዘመኑ ወቅት ለሚነሱ ጉዳዮች እልባት በመስጠት ረገድ እንዲያግዝ በማሰብ የተጠቀሰውን ግለሰብ ወይም ድርጅት በቀላሉ ማግኘት እንዲቻል ሲባል ነው። ይህ ተጨማሪ የማመልከቻ መረጃ የመኖሪያ አገልግሎት ሰጪው ጋር የሚቀመጥ ሲሆን ምሥጢር ተደርጎ ይያዛል። መረጃውን መስጠት በHUD ለሚታገዙ የመኖሪያ ቤቶች ፕሮግራም አሠራር መሠረታዊ ሲሆን ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት የሚከናወን ነው። በሕግ የተደነገገውን መስፈርት እና ፕሮግራም የሚያግዝ ሲሆን ማጭበርበር፣ ብክነት እና የአስተዳደር ጉድለት እንዳያጋጥም የሚደረገውን የአስተዳደር ቁጥጥርም ያግዛል። የወረቀት ሥራን ለመቀነስ በወጣው ደንብ መሠረት አንድ ኤጀንሲ መረጃ የማሰባሰብ ተግባር ሊያካሂድም ሆነ ስፖንሰር ሊያደርግ የማይችል ከመሆኑም ሌላ ስብስቡ የOMB ወቅታዊ የቁጥጥር ቁጥር ከሌለው በቀር ለመረጃ ስብስቡ ምላሽ መስጠት አይጠበቅበትም።

***የግል ገመና አጠባበቅን የሚመለከት መግለጫ፡*** የሕዝባዊ አስተዳደር ሕግ 102-550 (Public Law 102-550) የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት (Department of Housing and Urban Development (HUD)) በማጭበርበር ድርጊት ምክንያት የሚፈጠረውን የመረጃ ብክነት ለመከላከል ሲባል በHUD ጥቅም ላይ የሚውለውን መረጃ በሙሉ (ከማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር (SSN) በቀር) እንዲያሰባስብ ይፈቅዳል።